አብርሃም ሰሎሞን/ብሥራተ ገብርኤል/

# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

# አሐዱ አምላክ አሜን።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙትን የጾም ዓይነቶች እንዲሁም መቼ እና ለምን እንደሚጾሙ ከመጥቀሳችን በፊት ጾም ማለት ምን ማለት እንደሆነና መቼ እንደተጀመረ ማወቅ አስፈላጊ ስለሚሆን ከዚህ በታች መጠነኛ የሆነ ማብራሪያ እንሰጥበታለን፡-

## ጾም መቼ ተጀመረ፤ የማንስ ትእዛዝ ነው?

ጾም ማለት በምግብ እጦት መሰቃየት ወይም የሚበሉት ነገር አጥቶ መቅበዝበዝና መባከን ላለመሆኑ የአዳምና የሔዋን ኑሮ ቋሚ ምስክር ነው። ምክንያቱም በተድላ እና በፍሥሐ በመኖር ምድር ፍሬዋን ሳትከለክላቸው የሚበላው እና የሚጠጣው ነገር ሁሉ ከፊታቸው ነበራቸውና። ለአዳምና ለሔዋን ልዑል እግዚአብሔር የሚበሉትን ነገር ሳይከለክላቸው ከተወሰነ ምግብ ግን እንዳይበሉ አዝዞአቸዋል። እንግዲህ ጾም ማለት የሥጋ ፍላጎትን መግታት ማለት እንጂ ምግብ ማጣት አይደለም። ከጾም መታዘዝን፣ ራስ መግዛትን፣ የሥጋን ፍላጎት መቆጣጠርን፣ እግዚአብሔርን ማወቅን፣ ታማኝነትን እና በተስፋ መጠበቅን እንማራለን። ስለዚህም ጾም የተጀመረው በመጀመርያው የሰው ልጆች ፍጥረት በሆኑት በአዳምና በሔዋን ሲሆን ይኸንንም መልእክት ያስተላለፈው እግዚአብሔር ነው። አምላክ መሆንን ይሻ የነበረው የቀደመው እባብ ምኞቱና ሐሳቡ መክኖ ስለቀረበት ወደ አዳምና ሔዋን በመሔድ ያልተፈቀደላቸውን ነገር አይተው እንዲጓጉ ሁኔታዎችን አመቻቸላቸው። ከተከለከለው በመብላታቸው መታዘዝን ዘነጉ፣ ራስ መግዛትን ተዉ፣ የሥጋን ምኞት መቆጣጠርን ቸል አሉ፣ እግዚአብሔርን ማወቅን ሰነፉ፣ ታማኝነትን እና በተስፋ መጠበቅን ረሱ። እንግዲህ አለመታዘዛቸው ምን እንዳስከተለባቸው ለሁላችን ትምህርት ሆኖን እኛም በምንጾምበት ጊዜ ፈቃደ እግዚአብሔርን የምንፈጽም መሆን ይገባናል። ምንጊዜም ቢሆን ሥጋችንን ሊያስደስት እና እኛን ሊያሳስተን የሚመጣ ነገር መኖሩን መርሣት የለብንም። ትናንት አዳምና ሔዋንን ከእግዚአብሔር የለያየ እና ከመልካም ስፍራ እንዲወቱ ያደረገ ከሳሽ ዲያብሎስ ዛሬ በእኛ እቅፍ የለም ለማለት አይቻልም። ዕለቱን ባያስፈርድብን በመጨረሻው ዘመን ደጃፍ ያዘጋብናልና በምንጾምበት ጊዜ ራስን በመግዛት በፈሪሃ እግዚአብሔር መሆን ይጠበቅብናል።

## የጾም አስፈላጊነት፡-

ለሰው የሚያስፈልገውን ሁሉ ያዘጋጀ አምላክ ዘወትር መብላትና መጠጣት ብቻ ሰውን ስለማያንጸው የጾምን አስፈላጊነት ጠቅሶለታል። ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጾም ባስተማረበት አንቀጹ እንዲህ በማለት ያስተምረናል፡-

- ስትጦሙም፥ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፉሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጦም፥ በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ ፊትህንም ታጠብ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል። ማቴ.፮፡፲፮-፲፰

ሰው ደስተኛ ሆኖ እንዲኖር የሚያስፈልገው ገንዘብ ብቻ አይደለም። ሀብት እያላቸው የማይደሰቱ፣ ልጆች እያላቸው ባዶነት የሚሰማቸው፣ በመልካም ኑሮ እየኖሩ የጎደለባቸው፣ ተምረው እርካታ የሌላቸው ብዙዎች ናቸው። ከዚህ ቃል የምንረዳው ሰው ለፍጹም ደስታው የእግዚአብሔር እጅ እንጂ ምግብና መጠጥ ብቻ እንደማያስፈልገው ነው። ጌታችን በገዳመ ቆሮንቶስ በፈታኝ ዲያብሎስ ለቀረበለት ጥያቄ ከመጽሐፍ በመግለጽ ምላሽን እንደሰጠው ልብ ልንል ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ለሕዝበ እስራኤል የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስፈልጋቸው ሲነግራቸው እንዲህ ይለናል፡-

- በሕይወት እንድትኖሩ፥ እንድትበዙም፥ እግዚአብሔርም ለአባቶቻችሁ ወደ ማለላቸው ምድር ገብታችሁ እንድትወርሱአት፥ ዛሬ ለአንተ የማዝዘውን ትእዛዝ ሁሉ ታደርጉ ዘንድ ጠብቁ። አምላክህ እግዚአብሔር ይፈትንህ ዘንድ፥ በልብህም ያለውን ትእዛዙን ትጠብቅ ወይም አትጠብቅ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ፥ ሊያስጨንቅህ በእነዚህ በአርባ ዓመታት በምድረ በዳ የመራህን መንገድ ሁሉ አስብ። ሰውም ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ነገር ሁሉ በሕይወት እንዲኖር እንጂ ሰው በእንጀራ ብቻ በሕይወት እንዳይኖር ያስታውቅህ ዘንድ አስጨነቀህ፥ አስራበህም፥ አንተም ያላወቅኸውን አባቶችህም ያላወቁትን መና አበላህ። ዘዳ.፰፡፩-፫

# ሰባቱ አጽዋማት፡-

በቅድስት አገራችን በኢትዮጵያ መላው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በማኅበር የሚጾማቸው ሰባት አጽዋማት አሉ። እነርሱም፡-

፩ኛ- ጾመ ነቢያት/ የነቢያት ጾም(ጾመ ድኅነት)/፡-

- (ከጌታችን ከአምላካችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀን በፊት ባሉት አርባ ቀናት ውስጥ የሚጾም ነው።

፪ኛ- ጾመ ነነዌ/የነነዌ ጾም/፡-

- ሕዝበ ነነዌ የጾሙት እና መልስ ያገኙበት ለሦስት ቀናት የሚጾም ነው።

፫ኛ- ዐብይ ጾም/ጾመ ኢየሱስ/፡-

- ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ ለአርባ ቀናት የጾመው እና ከጾሙ መጀመርያ ያለው ሳምንት ጾመ ሕርቃል እንዲሁም የመጨረሻው ሳምንትን ሰሞነ ሕማማትን ጨምሮ ለስምንት ሳምንታት የሚጾም ነው።

፬ኛ- ጾመ ሐዋርያት/የሐዋርያት ጾም/፡-

- ከበዐለ ጰራቅሊጦስ ማግስት ከሰኞ ቀን ጀምሮ የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስና የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የመታሠቢያ በዓል እስከሚከበርበት ሐምሌ ፭ ቀን ድረስ ይጾማል። ይኸ ጾም እንደ ሌሎቹ አጽዋማት የተወሰነ ቁጥር የለውም። የትንሣኤ በዓል በመጀመርያው የሚያዝያ ወር ቀናት ሲውል እና በመጨረሻው የሚያዝያ ወራት ሲውል ቁጥሩ ከፍ እና ዝቅ ይላል። ሆኖም ግን በጣም ከፍ ሲል ለ፵፱ ቀናት በጣም ዝቅ ሲል ለ፲፭ ቀናት የሚጾም ነው።

፭ኛ- ጾመ ፍልሰታ/ጾመ ማርያም/፡-

- የእመቤታችን የትንሣኤዋ በዓል የሚከበርበት፤ ለሁለት ሳምንታት ያህል የሚፆም ነው።

፮ኛ- ጾመ ረቡዕና ዓርብ፡-

- ከትንሣኤ እስከ በዓለ ጰራቅሊጦስ ባሉት ረቡዕና ዓርብ ውጪ ጫመቱን በሙሉ ባሉት ረቡዕና ዓርብ ቀናት ይጾማል። ምክንያቱም ጌታን ለመያዝ ረቡዕ መክረው ዓርብ ስለሰቀሉት መከራውን ለማሰብ የሚጾም ነው።

፯ኛ- ጾመ ገሐድ/ጾመ ጋድ/፡-

- በየዓመቱ ከበዓለ ጥምቀት በፊት የሚጾም ነው። አንዳንዶች ከልደት በፊት ያለውን ቀን እንደ ገሐድ ጾም ሲቆጥሩት ይስተዋላል። ሆኖም ግን ያን ጊዜ ጾመ ድኅነት ተብሎ የሚጾምበት ወቅት በመሆኑ ከልደት በፊት ያለውን ቀን ጾመ ገሐድ ብሎ መጥራቱ አስፈላጊ አይደለም። ስለዚህም ጾመ ገሐድ ለአንድ ቀን የሚጾም ነው።

እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው ሰባት አጽዋማት ጊዜያቸው ሲደርስ የምንተነትናቸው ይሆናሉ። በዛሬው ዕለት ልናውቀው የሚገባን ከሰባቱ አጽዋማት አንዱ የሆነውን ጾመ ነቢያትን ይሆናል።

# ጾመ ነቢያት/ የነቢያት ጾም(ጾመ ድኅነት)/፡-

ይኸ ጾም የነቢያት ጾም በመባል የሚታወቀው ነቢያት ስለጾሙት ሲሆን ጾመ ድኅነት መባሉ ደግሞ ልዑል እግዚአብሔር የወደቀውን የሰውን ዘር ለማዳን የመጣበትን ቀን በማሰብ እና ዓለም ድኅነትን ያገኘበትን ሁኔታ ለማዘከር የሚጾም ጾም በመሆኑ ነው። ከኅዳር አጋማሽ እስከ ታኅሣሥ ፳፱ በዘመነ ማቴዎስ፣ ማርቆስ እና ሉቃስ እንዲሁም ከኅዳር አጋማሽ እስከ ታኅሣሥ ፳፰ በዘመነ ዮሐንስ የሚጾመው ይኸ ጾም ነቢዩ ሙሴ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፋትን አሥርቱ ትእዛዛትን ከመቀበሉ በፊት የጾመውን ጾም አብነት በማድረግ ነው። ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል ለመቀበል በጾም እንደተዘጋጀው ሁሉ እኛም ደግሞ ቃል ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ለመቀበል ፵ ቀናት እንጾማለን። በሕገ ልቡና ሲኖር ለነበረ ሕዝብ ሥርዓት ተበጅቶለት እና ሕግ ተጽፎለት በሕግ እንዲመራ የእግዚአብሔር ፍቃድ በመሆኑ ነቢዩ ሙሴ የተቀበለው ሕግ የእግዚአብሔርን ሕግ ነው።

# ሰማዮችን ቀድደህ ምነው ብትወርድ። ኢሣ.፷፬፡፩

ይኸንን ዓለም ለማዳን ያለኢየሱስ ክርስቶስ ምንም ዓይነት መፍትሔ እንደሌለ ገሐድ በመሆኑ ነቢዩ ኢሣይያስ ሰማዮችን ቀድደህ ምነው ብትወርድ በማለት ቃል ወልደ እግዚአብሔርን መማጸኑን ልብ ልንል ያስፈልገናል። የኢሣይያስ ጩኸትና ልመና ተሰምቶ ኢየሱስ ክርስቶስ ጊዜው ሲደርስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሊያድነን ወደ ምድር መጥቷል። ቃል ወልደ እግዚአብሔር ወደ ምድር እንደሚመጣ እና ዓለምን እንደሚያድን ነቢያት በተለየየ ስፍራ እና አጋጣሚ ሁሉ ገልጸዋል። በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም። አሞጽ ፫፡፯ ተብሎ እንደተጻፈ የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷል፤ የዲያብሎስን ሥራ ሊያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ በማለት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በሐዲስ ኪዳን ከመነገሩ በፊት የት ስፍራ እንደሚወለድ እና በተለያየ ሁኔታ በመገለጥ ዓለምን እንደሚያድን በስፋት ተገልጦአል። ነቢዩ ዳዊት በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው በማለት በዝማሬው ከተቀኘለት በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ በየት ስፍራ እንደሚወለድ እንደ ነቢዩ ሚክያስ በተናገረው ትንቢት እንዲህ ይለናል፡-

- እነሆ፥ በኤፍራታ ሰማነው፥ በዱር ውስጥም አገኘነው። ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን፤ እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን። መዝ.፻፴፩፡፮-፯
- አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል። ሚክ.፭፡፪

ነቢዩ ኢሳይያስም የጌታን መወለድና ወደ ምድር መምጣት በተናገረበት ሁለት ታዋቂ ምእራፎቹ እንዲህ በማለት አወላለዱንና ማንነቱን ይገልጻል፡-

- ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ኢሣ.፱፡፮
- ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች። ኢሣ.፯፡፲፬

ተዘግቶ የቆየው ገነት እንዲከፈት፣ ወድቆ የነበረው የአዳም ዘር እንዲነሣ፣ ጠፍቶ የነበረው ክብራችን እንዲመለስ ቃል ወልደ እግዚአብሔር ወደ ምድር በመምጣት ድኅነተ ነፍስ የምናገኝበትን ሕይወት ሊያድለን ተወለደ። በእነዚህ በአርባ ቀናት ውስጥ በሚደረገው ጾምና ሥርዓት ውስጥ ቤተ ክርስቲያናችን በስድስቱም ሳምንታት ውስጥ ነገረ ድኅነትን አስመልክቶ ትምህርቷን ታስተላልፋለች። በትምህርቷም የሰው ልጅን አወዳደቅና የዲያብሎስን ሥራ ስትገልጥ ለድኅነተ ዓለምም የእመቤታችንን ምክንያተ ድኅነት መሆን በሰፊው በማብራራት ከነምሳሌው ታስተምራለች። ከእነዚህ ሳምንታቶች የመጨረሻዎቹ ሦስት ሳምንታት ስብከት፣ ብርሃን እና ኖላዊ በመባል ይታወቃሉ።

# ዘመነ ስብከት ከታኅሣሥ ፯-፲፫፡-

በዚህ ወቅት ወይም በዚህ ሳምንት ቃል ወልደ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የሚመሰልባቸውን ምሳሌዎች በመጥቀስ ሰፊ ትምህርት ይሰጣል። ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን በብዙ ምሳሌዎች ይታወቃል የሚለውን ትምህርት ከማስተማር በፊት ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን መጠቀሱን የነገረንን የቅዱስ ወንጌል ቃልና የባለቤቱን ምስክርነት ማወቅ የተገባ ይሆናል። ነቢዩ ሙሴ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ላይ ስለመጻፉ ጌታችን እንዲህ ሲል ያስተምረናል፡-

- ✓ እኔ በአብ ዘንድ የምከሳችሁ አይምሰላችሁ፤ የሚከሳችሁ አለ፤ እርሱም ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው። ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር፤ እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና። መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ? ዮሐ.፭፡፵፭-፵፯

ሙሴ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የጻፋቸው እና ምስክርነቱን የሰጠባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ✓ በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ። ዘፍ.፫፡፲፭
- ✓ በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፥ የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፥ ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ፤ የአሕዛብ መታዘዝም ለእርሱ ይሆናል። ውርንጫውን በወይን ግንድ ያስራል፥ የአህያይቱንም ግልገል በወይን አረግ፤ ልብሱን በወይን ያጥባል፥ መጎናጸፊያውንም በወይን ደም። ዓይኑም ከወይን ይቀላል፤ ጥርሱም ከወተት ነጭ ይሆናል። ዘፍ.፵፱፡፲-፲፪
- ✓ አየዋለሁ፥ አሁን ግን አይደለም፤ እመለከተዋለሁ፥ በቅርብ ግን አይደለም፤ ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል፥ ከእስራኤል በትር ይነሣል፥ ዘኁ.፳፬፡፲፯

# ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን የተነገሩ ምሳሌዎችን በአምስት አበይት ክፍሎች ከፍለን እንመለከታቸዋለን፡-

፩ኛ፡- የቅዱሳን ሰዎች ምሳሌነት
፪ኛ፡- የእንስሳት ምሳሌነት
፫ኛ፡- የተለያዩ ሁኔታዎች ምሳሌነት
፬ኛ፡- የመጽሐፍ ቃል ምስክርነት
፭ኛ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን

## ፩ኛ፡- የቅዱሳን ሰዎች ምሳሌነት

### ሀ/ የአዳም ምሳሌነት፡-

በአንድ አዳም ኃጢአት ዓለምን በመግዛቱ በአንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ወደ ጽድቅ በመመለሱ ተመሳሳይነት አላቸው።

- ✓ ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤... በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ።...በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ። እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ። በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ። ሮሜ.፭፡፲፪-፲፱
- ✓ አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል። ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና። ፩ኛ ቆሮ.፲፭፡፳-፳፪
- ✓ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፥ መንፈሳዊ አካል ይነሣል።...እንዲሁ ደግሞ። ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ። ነገር ግን አስቀድሞ ፍጥረታዊው ቀጥሎም መንፈሳዊው ነው እንጂ መንፈሳዊው መጀመሪያ አይደለም። የፊተኛው ሰው ከመሬት መሬታዊ ነው፤ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ ነው። መሬታዊው እንደ ሆነ መሬታውያን የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው፥ ሰማያዊው እንደ ሆነ ሰማያውያን የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው። ፩ኛ ቆሮ.፲፭፡፵፬-፵፰

### ለ/የመልከጼዴቅ ምሳሌነት፡-

ለዘላለም ካህን ነህ ተብሎ ስለተነገረ መልከጼዴቅ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ቀርቧል። ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ ነውና። መልከጼዴቅ ይዞት የተገኘው ኅብስት እና ወይን በጌታ ሥጋና ደም መመሰሉ።

- ✓ እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ፥ እግዚአብሔር ማለ አይጸጸትም። መዝ.፻፱፡፬
- ✓ ከተፈጸመም በኋላ በእግዚአብሔር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ ስለ ተጠራ፥ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው። ዕብ.፭፡፱-፲
- ✓ የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ፤ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ። ዘፍ.፲፬፡፲፰
- ✓ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሬ አልጠጣውም። ማቴ.፳፮፡፳፱

### ሐ/የይስሐቅ ምሳሌነት፡-

የይስሐቅ መታዘዝና የሚሠዋበትን እንጨት መሸከም፤ እስከ ሞት ድረስ ለአባቱ መታዘዙ፤ በይስሐቅ ምትክ የበግ መሥዋዕት መቅረቡ፤ አብርሃም የሚወደውን አንድ ልጁን ለሞት አሳልፎ መስጠቱ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ሞት ድረስ የመታዘዙን ነገር ይመስልልናል።

- ✓ አብርሃምም የመሥዋዕቱን እንጨት አንሥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከመው፤ እርሱም እሳቱንና ቢላዋውን በእጁ ያዘ፥ ሁለቱም አብረው ሄዱ። ዘፍ.፳፪፡፮
- ✓ እግዚአብሔር ወዳለውም ቦታ ደረሱ፤ አብርሃምም በዚያ መሠዊያውን ሠራ፥ እንጨትንም ረበረበ፤ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊያው በእንጨቱ ላይ አጋደመው። ዘፍ.፳፪፡፱
- ✓ አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስተ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው። ዘፍ.፳፪፡፲፫
- ✓ ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፥ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፤ ፩ኛ.ጴጥ.፫፡፲፱-፳

## መ/የያዕቆብ ልጅ የዮሴፍ ምሳሌነት፦

ወንድሞቹ ዮሴፍን መጥላታቸው፤ ልብሱን መግፈፋቸው፤ ለነጋዴዎች በሃያ ብር መሸጣቸው፤ የሐሰት ምስክር መመስከራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ በመከራው ሰዓት ያጋጠሙትን ነገሮች ስለሚመስል ዮሴፍ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ይቆጠራል።

- ✓ ወንድሞቹም አባታቸው ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ እንዲወደው ባዩ ጊዜ ጠሉት፥ በሰላም ይናገሩትም ዘንድ አልቻሉም።..ወንድሞቹም። በእኛ ላይ ልትነግሥብን ይሆን? ወይስ ልትገዛ ይሆን? አሉት። እንደ ገናም ስለ ሕልሙና ስለ ነገሩ ይልቁን ጠሉት። ዘፍ.፴፯፡፬ እና ፰
- ✓ ሌላ ሰው ያላደረገውን ሥራ በመካከላቸው ባላደረግሁ፥ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን እኔንም አባቴንም አይተውማል ጠልተውማል። ነገር ግን በሕጋቸው። በከንቱ ጠሉኝ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው። ዮሐ.፲፭፡፳፬-፳፭
- ✓ እንዲህም ሆነ፤ ዮሴፍም ወደ ወንድሞቹ በቀረበ ጊዜ የለበሳትን በብዙ ኅብር ያጌጠቺቱን ቀሚሱን ገፈፉት፤ ዘፍ.፴፯፡፳፫
- ✓ ጭፍሮችም ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ልብሶቹን ወስደው በአራት ከፋፈሉት፤ እጀጠባቡን ደግሞ ወሰዱ።...ስለዚህ እርስ በርሳቸው። ዕጣ እንጣጣልበት እንጂ አንቅደደው ተባባሉ። ይህም። ልብሴን እርስ በርሳቸው ተከፋፈሉ በእጀ ጠባቤም ዕጣ ተጣጣሉበት የሚለው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው። ዮሐ.፲፭፡፳፫-፳፬
- ✓ ለእስማኤላውያንም ዮሴፍን በሀያ ብር ሸጡት፤ ዘፍ.፴፯፡፳፰
- ✓ በዚያን ጊዜ የአስቆሮቱ ይሁዳ የሚባለው ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ወደ ካህናት አለቆች ሄዶ። ምን ልትሰጡኝ ትወዳላችሁ እኔም አሳልፌ እሰጣችኋለሁ? እነርሱም ሠላሳ ብር መዘኑለት። ማቴ. ፳፮፡፲፬-፲፭

# ፪- የእንስሳት ምሳሌነት፦

በብሉይ ኪዳን በካህናት ይቀርብ የነበረው የበደል ማስተሰርያ እንስሳት ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን በደል ለማጥፋት እራሱን መሥዋዕት አድርጓልና። ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንመልከት፦

- ✓ ተጨነቀ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። ኢሳ.፶፫፡፯
- ✓ ሙሴም ስለ ሕዝቡ ጸለየ። እግዚአብሔርም ሙሴን። እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል፤ የተነደፈውም ሁሉ ሲያየው በሕይወት ይኖራል አለው። ሙሴም የናሱን እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ፤ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ። ዘኁ.፳፩፡፰-፱
- ✓ ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዮሐ.፫፡፲፬-፲፮

# ፫- የተለያዩ ሁኔታዎች ምሳሌነት፦

ኢየሱስ ክርስቶስ በብርሃን፣ በበር፣ በፀሐይ፣ በእንጀራ፣ በቤተ መቅደስ፣ በመንገድ፣ በማዕዘን ራስ፣ በሥር፣ በወይን ግንድ፣ በሕይወት ውኃ፣ በንጋት ኮከብ ይመሰላል። ከዚህ በታች የተገለጹትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ልብ ብለን እንመልከት።

- ✓ ደግሞም ኢየሱስ። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው። ዮሐ.፰፡፲፪

- በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል። ዮሐ.፲፡፱
- ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም፥ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ። ራእ.፳፪፡፭
- ኢየሱስም እንዲህ አላቸው። የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም።...ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው። ዮሐ.፮፡፴፭ እና ፶፩
- ኢየሱስም መልሶ። ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው። ስለዚህ አይሁድ። ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፥ አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር። ዮሐ.፪፡፲፱-፳፩
- ኢየሱስም። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። ዮሐ.፲፬፡፮
- በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ኤፌ.፪፡፳
- እንግዲህ ክብሩ ለእናንተ ለምታምኑት ነው፤ ለማያምኑ ግን አናጢዎች የጣሉት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ የዕንቅፋትም ድንጋይ የማሰናከያም ዓለት ሆነ፤ የማያምኑ ስለ ሆኑ በቃሉ ይሰናከሉበታልና፤ ለዚህ ደግሞ የተመደቡ ናቸው። ፩ጴጥ.፪፡፯-፰
- እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፥ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ። ራእ.፳፪፡፲፮
- እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ ገበሬውም አባቴ ነው። ዮሐ.፲፭፡፩
- እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፥ እኔ የምሰጠው ውኃ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት። ዮሐ.፬፡፲፬

# ፬ኛ፡- የመጽሐፍ ቃል ምስክርነት

በብሉይ ኪዳን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው በሐዲስ ኪዳን እንዴት ፍጻሜውን እንዳገኘ የሚያስረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ? ተብሎ በኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው እና የተጻፈው ቃል አስቀድሞ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጻፈ ጽሑፍ መኖሩን አጥብቆ ለመግለጽ የተነገረ ነው።

# ፭ኛ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን

ስለ አምላካችን ስለ ጌታችን እና ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ትውልድ ሐረጉ፣ ስለ ትውልድ ቦታው፣ ከመጥምቁ በኋላ ስለመምጣቱ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ስለመግባቱ፣ በወዳጆቹ ተላልፎ ስለመሰጠቱ፣ በከሳሾቹ ፊት ዝም ስለማለቱ፣ ከወንበዴዎች ጋር ስለመሰቀሉ፣ በብር ስለመሸጡ፣ ልብሱን ስለመካፈላቸው፣ በመስቀል ላይ አምላኬ አምላኬ ስለማለቱ፣ ጎኑን በጦር ስለመወጋቱ፣ በስቅለቱ ጊዜ ስለመጨለሙ እና ስለሌሎችም ሁኔታዎች አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ተጽፎ የነበረው የትንቢት ቃል በሐዲስ ኪዳን ፍጻሜን አግኝቷል። ስለዚህም በዚህ በዘመነ ስብከት እነዚህ ሁሉ ትምህርቶች ከሰፊ ማብራሪያ ጋር ይሰጣሉ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

አብርሃም ሰሎሞን slat6@yahoo.com

____________________//____________________

ብርሃን ከታኅሣሥ ፲፬-፳፡- እና ኖላዊ ከታኅሣሥ ፳፩-፳፯፡- ይቀጥላል...